# Learning by Ear 2013

## መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE EIGHT: እንኳን ወደ ሴትነት በደህና መጣሽ

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Yann Durand**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ሙላቱ MOVES WITH HIS FAMILY TO A BETTER HOUSE**

- **ሙላቱ (M, 45)**
- **ምህረት (F, 15)**

**SCENE 2: ዳንኤል ካሳሁን SKYPES WITH HIS FATHER IN LABORIA**

- **ዳንኤል (M, 16)**
- **አቶ ካሳሁን (M, 55)**

**SCENE 3: ምህረት GETS HER FIRST PERIOD IN CLASS**

- **GROUP OF STUDENTS (M/F, 15/16)**
- **ንጉሴ (M, 16)**
- **ዳንኤል (M, 16)**
- **ትዕግስት (F, 15)**
- **ምህረት (F, 15)**
- **ርዕሰ መምህርት ሰብለ (F, 50)**

1. **INTRO - NARRATOR:**

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ታዳሚዎች፤ ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ሶስት ወጣቶች የህይወትን ትክክለኛ አቅጣጫ ለማግኘት ሲጥሩ የሚያሳያን ተከታታይ የራድዮ ድራማ ክፍል ስምንት ነዉ። እስቲ ለትውስታ ያህል ባለፈዉ ዝግጅት ምን እንደተከሰተ እናስታዉስ ,,,

ዳንኤል ለሀገሩ ሙሉ በሙሉ እንግዳ ነው፡፡ በጎረቤት ሀገር ላቦሪያ የማዕድን ድርጅት ባለቤት የሆኑት አባቱ፤ ወራሹን ልጃቸዉን ኪሲምባ ውስጥ መልካም ስም ባላለው ቦንጎ አካዳሚ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለማስተማር ወስነዋል፡፡

2. **አቶ ካሳሁን (EP 04, 101):** " ዳንኤል እኔ ስሞት ንግዱን የምትረከበው አንተ ነህ፡፡ ስለዚህ ከአሁኑ ማሰብ እና ኃላፊነት እንዲሰማህ ያስፈልጋል፡፡"

3. **ዳንኤል:** "አባዬ በዚህ ጉዳይ ላይ ሺህ ጊዜ ነው የተነጋገርነው! እኔ የማዕድን ስራውን አልወድም ብዬሃለሁ"

በተለይ ደግሞ ዳንኤል በክፍሉ ዉስጥ አብራው ያለችዉ ጎበዟ እና ቆንጆዋን ምህረትን ካየበት ጊዜ አንስቶ ለማዕድን ስራው ፍላጎት የለውም ። የእርሷ አድናቂ እርሱ ብቻ አለመሆኑ ደግሞ የበለጠ መጥፎ አጋጣሚ ሆኖበታል፡፡ ምህረት ላይ የክፍል ጓደኛው ንጉሴም እያደባ ነዉ፡፡

4. **PEN SCRIBBLING ON PAPER**

5. **ንጉሴ (EP 05, 50):** “የእኔ ውድ ምህረት፡፡ ከየት እንደምጀምር አላውቅም፡፡ ምን እንደሚሰማኝ ልገልጽልሽ ትክክለኛ ቃል ስፈልግ ነበር,,,,፡፡”

አሁን ምህረት አዕምሮ ዉስጥ የሚጉላላዉ ሌላ ነገር ነዉ፡፡ በሚቀጥለዉ ቀንም ምህረት ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ስትመለስ እናቷ፣ ሉሊት፣ ወለሉ ላይ እራሷን ስታ ክፉኛ እየደማች አግኝታታለች፡፡ ወ/ሮ ሉሊት ሴት ልጅ መገላገልዋን እና ህጻኗ መሞቷን ለልጅዋ ለምህረት ነግራታለች ፡፡ ይህ ግን እውነት አልነበረም፡፡ እውነታው የምህረት አባት፣ ሙላቱ፣ ህጻኗን ከከተማው ሀብታሞች አንዱ ለሆኑት፣ ለአቶ መኩሪያ ሸጧታል፡፡ አቶ መኩሪያም ህፃንዋን አሁን በህገ ወጥ መንገድ በጉዲፈቻ ወስደዊታል፡፡ ዛሬ የምናደምጠዉ ስምንተኛው ክፍል ድራማ ፣ “እንኳን ወደ ሴትነት በደህናመጣሽ” በሚል ርዕስ ይዞአል፡፡ አሁን ከነምህረት እና ከአባቷ፣ አቶ ሙላቱ፣ ጋር በታንዲካ ጎስቋላ መንደር በሚገኘዉ ቤታቸው ውስጥ እንገኛለን፡፡ ሁለቱም እቃቸዉን እየሸከፉ ናቸዉ…

## SCENE 1: MOVES WITH HIS FAMILY TO A BETTER HOUSE

6. **SLUM ATMO - INTERIOR**

7. **SFX: KITCHEN UTENSILS BEING PACKED INTO A BOX**

8. **ሙላቱ:** ምህረት፣ እነዚህያን ሳህኖች በደንብ በጥንቃቄ፡ አሽጊያቸው፡፡

9. **ምህረት:** አባ ወደየት ልንሄድ ነው? ምንም የነገርከኝ ነገር እኮ የለም፡፡.

10. ሙላቱ: ለእናትሽ እንዳትነገሪያት። ምስጢር ነው! ከሆስፒታል በቀጥታ ወደ አዲሱ ቤታችን እዉስዳታለሁ። እመኚኝ እሺ? ከዚህ የተሻለ መኖርያ ቤት ነው።

11. ምህረት: እሺ፣ አምኜሀለሁ አባ።

12. ሙላቱ: ዛሬ ደግሞ ግርጥት ብለሽብኛል! ደህና ነሽ?

13. ምህረት: እኔ እንጃ እንግዳ ስሜት ይሰማኛል... ልክ ሆዴ እንደተነፋ ወይም እንደሆነ ነገር ይሰማኛል ። እቃውን ሳሽግ ተንቀራፈፍኩብህ አይደል አባ! ይቅርታ!

14. SFX: KITCHEN UTENSILS BEING PACKED INTO A BOX

KW BEGIN

15. ምህረት: አባዬ...እ ስለእዛ ያሰብኩ ነበር... ትንሿን እህቴን የት እንደቀበርካት ባዉቅ ደስ ይለኛል። የመቃብሯን ቦታ ማየት እፈልጋለሁ።

16. ሙላቱ: (angry) ለምን?,,እ,,ምን,,ያደርግሻል? እህ? እሺ,,,መቃብሩን አየሽው... ከዚያስ! ያ ወደ ህይወት ይመልሳታል?

17. ምህረት: እንዳው ዝም ብዬ እዚያ ሄጄ ብሰናበታት ጥሩ ነው ብዬ አስቤ ነው።

18. ሙላቱ: የመጨረሻ ስንብት? የአንድ አገር መሪ ርዕሰ ብሄር እኮ አይደለችም። አይኖቿን ሳትገልጥ ነው ህይወትዋ ያለፈዉ። በሰላም እንድታርፍ ልትተያት አትችይም?

19. ምህረት፡ (agrees) ልክ ነህ። እንድታርፍ መተው አለብኝ። የእህቴን ነፍስ በሰላም ያሳርፍልኝ።

20. ሙላቱ፡ አሁን እቃውን እናውጣ። መኪናዉ እየጠበቀን ነው።

21. ምህረት፡ (reacts to pain) ወይኔ... አንድ ደቂቃ ልረፍ። ሆዴ እየቆረጠኝ ነው።

**KW END**

22. ሙላቱ፡ ምናልባት የበላሽው ምሳ እንዳይሆን ችግሩ።

23. ምህረት፡ ልክ ነው፣ ምን አልባት።፣ እኔ እንጃ የሆነ እንግዳ ነገር ይሰማኛል። እስከ ነገ ጠዋት ይሻለኛል ብዬ እገምታለሁ፤ ከትምህርት ቤት መቅረት አልፈልግም።

24. ሙላቱ፡ ነገ እናትሽ ከሆስፒታል ስትወጣ ብዙ እርዳታና ድጋፍ ያስፈልጋት ይሆናል!,,, ቆይ እነዚያን ወንበሮች እኔ ልሸከም፣ አንቺ ደግሞ ትንንሾቹን ሳጥኖች ውጪ አውጫቸው።

25. **SFX: ሙላቱ ACTS CARRYING HEAVY STUFF**

26. **MUSIC INTERLUDE**

**SCENE TWO: ዳንኤል ካሳሁን SKYPES WITH FATHER LIVING IN LABORIA**

**27. DORMITORY ATMO, FAINT TRAFFIC NOISE FROM OUTSIDE**

**28. SFX: INTERNET CALL RINGING**

29. ዳንኤል: ሃሎ …አባዬ፣ ይሰማሀል?

30. አቶ ካሳሁን: አዎ፣ ዳኒ ይሰማኛል ! እንዴት ነህ?

31. ዳንኤል: ኪሲ ባዶ ነዉ እንጂ ደህና ነኝ። እቤት ሁሉም ነገር ደህና ነው?

**KW BEGIN**

32. አቶ ካሳሁን: አይ ሁሉ ነገር ደህና አይደለም። ግን አትጨነቅ። አባትህ ሁኔታውን ይቆጣጠረዋል።

33. ዳንኤል: እማዬ እንዴት ነች?

34. አቶ ካሳሁን: ደህና ናት። ብቻ በአዲሱ የኑሮ ሁኔታ እንዴት እንደምትዘልቅ በማሰብ በጣም ትጨነቃለች። እናትህን ታውቃታለህ…ለማንኛውም፣ ክፍልህን በኢንተርኔት እንደምታሳየኝ ቃል ገብተህልኝ ነበር?

35. ዳንኤል: ዉይ አባ ትረሳዋለህ ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበር። እሺ እንደዝያ ከሆነ ቆይ ,,እ,እ, ተዘጋጅቻለሁ፤ ዌብካሜራዩን ላብራ!

**36. SFX: MOUSE CLICK**

37. ዳንኤል: አሁን እታይካለው?

38. አቶ ካሳሁን: **(pleased)** አሀ፣ የእኔ ዳንኤል ይታየኛል ያዉና። ሃ ሃ ከሳ ብለሀ ፣ ክብደት ቀንሰሃል! ለመሆኑ በደንብ ትበላለህ?

39. ዳንኤል፡ (ignoring his father's comment) ይኸዉልህ ክፍሌ ይህንን ይመስላል። አልጋዬ፣ እዛ ጋር ነው። እዚያ ጋር ደግሞ የመጽሐፍ መደርደሪያዬ አለኝ። እና ጥጉ ላይ ያለው የመታጠቢያ ክፍሌ ነው። የማንበቢያ ጠረጴዛው እና ወንበሩ አሁን ያለሁበት ነው። እዛ ጋር ያለው በር የእኔን ክፍል ከበለጠ ክፍል የሚለየው ነው። በለጠ አብሮኝ የሚኖር ጥሩ ልጅ ነዉ፣ ጥሩ ጓደኛሞች እንደምንሆን አስባለሁ። ይኸው እንግዲህ አየኸው።

40. አቶ ካሳሁን፡ ይኸው ነው? ለእኔ ግን የሆነ የእርግብ ጎጆ ነው የመሰለኝ! እና ያንን ሁሉ ገንዘብ እየከፈልኩ ያለሁት ለእንዲህ አይነቱ መኖርያ ነው የምትለኝ? ዳንኤል አንተ ብትፈልግ ኖሮ አውሮፓ በሚገኝ ትምህርት ቤት ላዘዋውርህ እንደምችል ታውቃለህ!

41. ዳንኤል፡ (rejecting strongly) አይ አይ አይሆንም፣ አይሆንም፣ አባዬ! ሌላ ቦታ የትም መሄድ አልፈልግም። ይህንን ቦታ ወድጄዋለሁ። ጥሩ ትምህርት ቤት ነው።.

42. አቶ ካሳሁን፡ ነው ጥሩ...ፍቅር የያዘህ ትመስላለህ።

43. ዳንኤል፡ ማን? እኔ? አይደለም! ምን ማለትህ ነው? እኔ ...እኔ...

44. አቶ ካሳሁን፡ ማለቴ ከሀገሩ ጋር ፍቅር ይዞሀል! ለማንኛውም ሀገርህ እዚህ መሆኑን እና ሀገርህም እንደምትፈልግህ አስታውስ።

45. ዳንኤል፡ እሺ፣ አውቃለሁ። አባዬ፣...እንዷት ሳንቲም እንኳ ስለሌለኝ መፍትሄ ልትፈልግልኝ ይገባሀል....

**KW END**

46. **አቶ ካሳሁን:** ዳንኤል! ልታከስረኝ ነው። ይሄ በዚህ አመት የሚሰጥህ የመጨረሻው ክፍያ ነዉ፤ እንዴት መቆጠብ እንደሚቻል ተማር። ገባህ አይደል? ነገ ጥቂት ገንዘብ እልክልሀለሁ።

47. **ዳንኤል:** አመሰግናለሁ አባ። በእውነት። አሁን ከሰዓት በኋላ ወደሚሰጠው ትምህርት መሄድ አለብኝ ግን (affectionately) ...አእህ፣ ቤት በጣም ናፍቆኛል። .

48. **አቶ ካሳሁን:** (affectionately) ዳንኤል አንተንም ቤተሰቡ ሁሉ ናፍቆአል። እሺ አሁን እኔም መሄድ አለብኝ! ዳንኤል ብዙ አትጨነቅ። ገንዘቡን እንደላኩ እደውልልሀለሁ። በል እስከዝያዉ ደህና ሁን።

49. **SFX: INTERNET CALL DISCONNECTED**

50. **MUSIC INTERLUDE**

51.

**<u>SCENE 3: ምህረት GETS HER FIRST PERIOD IN CLASS</u>**

52. **SFX: CLASSROOM AMBIENCE**

53. **ንጉሴ:** (shouts out loud) ሁላችሁም ጸጥ በሉ! ርዕሰ መምህርቷ ባዮሎጂ ትምህርት ሊያስተምሩን በየትኛውም ጊዜ ይመጣሉ።

54. **SFX: STEPS ዳንኤል COMES IN**

55. **ንጉሴ:** ዳንኤል አርፍደሃል፤

56. ዳንኤል: (arrogantly) ሄሄ ፣ ንጉሴ። በቃ ትኩረት ለመሳብ አንድም የሚያመልጥህ አጋጣሚ የለም አይደል? እና ምን ይጠበስ? ርዕሰ መምህርቷ ይመጣሉ ይሄዳሉ! አንተም እንደዚያው፣ ንጉሴ፡ ለዘላለም የክፍሉ አለቃ መሆን አትችልም፣ ታውቃለህ።

57. SFX: CLASS REACTS WITH "AH'S" AND "OH'S"

58. ንጉሴ: በቃህ ዳንኤል! ይሄየማይረባ አስተያየትህ እና መጥፎ ባህሪ አፍንጫዬ ላይ ደርሷል።። ከዚህ ክፍለ ጊዜ በኋላ ቀጥ ብዬ ሄጄ ስለአንተ ለርዕሰ መምህርቷ እናገራለሁ።

59. ዳንኤል: ተናገር ምን ይመጣል? ደግሞ ምንም ማለት አይደለም። ለምን ለትምህርት ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አትናገርብኝም? ወይም እንዳውም ለአባትህ ለምን አትነግራቸዉም?

60. ንጉሴ: (furious) አሁን ገና ድንበርሽን አለፍሽ! እንደ ወንድ እዚሁ ይዋጣልናል!

61. ዳንኤል: በላ ቀጥል! እንደውም ይቺን አጋጣሚ እየጠበቅሁ ነበር።

62. SFX: DESKS AND CHAIRS BEING PULLED ASIDE / FIGHT BETWEEN BOYS

63. ትዕግስት: (frantic)ምህረት! ተመልከቺ ወንዶችሽን ከመደባደባቸው በፊት አታስቆሚያቸውም?

64. ምህረት: (gently) ዳንኤል ፣ ንጉሴ! ምነው እንደ እድሜያችሁ ብትሆኑ አይሻላችሁም? (suddenly shrieks with stomach pain) አሀ፣ ሆዴን! በእውነት በጣም አመመኝ! ትዕግስት፣ እባክሽ እርጂኝ... ኡኡኡ!

65. SFX: DESKS MOVING AS ንጉሴ AND ዳንኤል FIGHT

66. ትዕግስት: ምህረት፣ ምን ሆንሽ? አይዞሽ ቁጭ በይ።

67. SFX: CHAIR BEING PULLED

68. ምህረት: ምን እንደሆንኩ አላውቅም። ከጠዋት ጀምሮ ሆዴን ይቆርጠኛል! ግን እንደ ተራው የሆድ ህመም አይነት አይደለም...

69. ትዕግስት: ምንአልባት የወር አበባሽ ይሆን?

70. ምህረት: ምኔ? አሀ፣ የወር አበባዬ «ፔሪዴ» ማለትሽ ነው?

71. ትዕግስት: አዎ። የእኔ የመጣዉ ልክ 12 ዓመት ሲሞላኝ ነዉ! ቆይ ምህረት አሁን ወደ መጸዳጃ ቤት እወስድሻለሁ።

72. SFX: FOOTSTEPS LEAVING

73. CROSSFADE BATHROOM: ECHOEY SOUND

74. SFX: TOILET CUBICLE DOOR CLOSING

75. SFX: CLOTH RUSTLE

76. ምህረት: (behind the door) ትዕግስት! እየደማሁ ነኝ!

77. ትዕግስት: አየሽ፣ ፔሬድሽ ማለት የወር አበባሽ ነው። እንኳን ደስ አለሽ፣ ምህረት። አሁን ሴት ሆነሻል! (chuckles)

78. **ምህረት:** ምን ላድርግ?

79. **SFX: ትዕግስት RUMMAGING AROUND IN HER BAG**

80. **ትዕግስት:** ቆይ፣ ሞዴስ አለኝ! (short pause) የውልሽ! ፓንትሽ ውስጥ አድርጊው።

81. **ምህረት:** ኦህ፣ አመሰግናለሁ!

82. **SFX: CLOTH RUSTLE**

83. **SFX: BATHROOM DOOR OPENED FORCEFULLY**

84. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** ትዕግስት! እዚህ ታውደለድያለሽ! እሺ ምህረትስ የት ናት?

85. **TOILET CUBICLE DOOR OPENS**

86. **ምህረት:** (coming out of the toilet) አቤት እዚህ ነኝ

87. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** ለምን ከክፍል ወጣችሁ? ደግሞም ሁለታችሁም የት እንደሄዳችሁ እንኳን ማንም አላወቀም!

88. **ትዕግስት:** ይቅርታ መምህርት ዘውዲቱ። የወጣነዉ ምህረት ፔሬዷ መጥቶባት ነው።

89. **ርዕሰ መምህርት ሰብለ:** ምህረት፣ እውነት ነው?

90. **ምህረት:** (ashamed) ምምህ

91. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: (reassuring)እህ፣ምህረት፡፡ ማፈር አይገባሽም! እንኳን ወደ ሴትነት በደህና መጣሽ፡፡ አሁን ይህ ምን ማለት እንደሆነ ታውቂያለሽ? መጸነስ እና ማህጸንሽ ውስጥ ልጅ ማርገዝ ትችያለሽ ማለት ነው፡፡ ምን ይሰማሻል?

92. ምህረት: አሁን ደህንነት ይሰማኛል ፡፡ አመሰግናለሁ፡፡ መምህርት

93. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: ምንም አይደለም፡፡ እኛ ሴቶች እርስ በእርሳችን መረዳዳት አለብን፡፡ ግን ምህረት፣ ይህ ለምን እንደተከሰተ ገብቶሻል?

94. ምህረት: ይመስለኛል…ግን እርግጠኛ አይደለሁም…

95. ርዕሰ መምህርት ሰብለ: አሁን ሜናርክ የሚባለው ደረጃ ላይ ነው የደረስሽው፡፡ ይህ የሴት ልጆች የመጀመሪያው ማንስተሬሽን «የወር አበባ» ነው፡፡ ከዚህ በኋላ በየወሩ አንድ ጊዜ ስለሚመጣ መዘጋጀት ያስፈልገሻል፡፡

96. ምህረት በእውነት? ግን በየወሩ? ምን ያህል ጊዜ ይቆያል?

97. ርዕሰ መምህርት ሰብለ መናገር ይከብዳል፡፡ እያንዳንዷ ሴት የራሷ ኡደት አላት፡፡ መጀመሪያ ላይ ጊዜው ይዛባ ይሆናል፡፡ ወሲብ እስካልፈጸምሽ ድረስ መጨነቅ አይገባም፡፡ ይህ የሚሆነው ሰውነትሽ ከለውጡ ጋር ለመላመድ ሲጥር ነው፡፡ ትልቁ ነገር እራስሽን መጠበቅ ነው፡፡ ገባሽ አይደል?

98. ምህረት አዎ፣ እንደነዚህ አይነት የተወሰኑ ሞዴሶችን እይዛለሁ……

99. ርዕሰ መምህርት ሰብለ ያን ማለቴ አይደለም! የምናገረው ስለ ወሲብ ነው፣ ምህረት። አሁን ልትጸንሺ ስለምትችዪ የወሊድ መከላከያ መጠቀም አለብሽ። ወሲብ እስካልፈጸምሽ ድረስ መጨነቅ አይገባሽም። ወሲብ ግን ከፈጸምሽ ራስሽን ለእርግዝና አጋለጥሽ ማለት ነው።.

100. ምህረት ይህ ሁሉ ህመምስ፣ የሆድ ቁርጠቱ እና የራስ ምታቱስ?

101. ርዕሰ መምህርት ሰብለ ጥሩ፣ እነዚህ ፔሬድሽ በመጣ ቁጥር ከሚታዩ የተወሰኑ ምልክቶች መካከል ናቸው። የሆድ ቁርጠቱ የተለመደ ነው፡ ፡ ሁል ጊዜም የህመም ማስታገሻ መውሰድ ግን መጥፎ ነው። አትጨነቂ-የተፈጥሮ ስለሆነ፣ እመኚኝ ተፈጥሮ ለራሷ በደንብ ትጨነቃለች። ፔሬድሽ ሲመጣ ውጥረት፣ ቁጣ ቁጣ፣ ብስጭት ሊሰማሽ እንደሚችል አስተውይ። አትጨነቂ-ምልክቶቹ ረጅም ጊዜ አይቆዩም

102. ምህረት አመሰግናለሁ፣ ወ/ሮ ዘውዲቱ። እናቴ ከዚህ የበለጠ ባዘጋጀችኝ ደስ ይለኝ ነበር።

103. ርዕሰ መምህርት ሰብለ እናትሽን አትውቀሻት። እናቴም ስለዚህ ነገር ፈጽሞ ነግራኝ አታውቅም። ግን አሁን ወደ ቤት ብትሄጂ ጥሩ ይመስለኛል። ይህንን ነገር ለመልመድ ትንሽ ጊዜ የሚያስፈልግሽ ይመስለኛል፣ አይመስልሽም። ጥያቄ ካለሽ ግን እኔ ጋር ለመምጣት ቅንጣት ታህል እንዳትጠራጠሪ እሺ?

104. ምህረት፡ እሺ።

**105. ርዕሰ መምህርት ሰብለ በይ አሁን፣ ትዕግስት፣ ወደ ክፍል እንግባ፡፡ (ironically)**

**አንቺም የክፍል ጓደኞችሽም ትምህርቱን ለመቀጠል እንደቋመጣችሁ እርግጠኛ ነኝ፡፡**

**106.ትዕግስት: (lethargic) ልክ ነዎት!**

**107. <u>OUTRO/MODERATOR:</u>**

**በዚሁ መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘዉን የዶይቸ ቬለ ተከታታይ ትምህርታዊ ድራማ ስምንተኛ ክፍል እናበቃለን። ምህረት አሁን ወደ ሴቶች ዓለም ተቀላቅላለች፤ ግን በጸባይዋ እና በሰዉነቷ ላይ የሚመከሰተዉን ለዉጥ እንዴት ትቀበለዉ ይሆን? የእነዚህን መልሶች በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ ይከታተሉ። ያለፉትን ድራማ ክፍሎች ማድመጥ ከፈለጋችሁ አልያም ድራማዉን በግል ማህደር መገልበጥ ከፈለጋችሁ በድረ-ገጽ አድራሻችን <u>dw.de/lbe</u>.ላይ ያገኛሉ። በፊስቡክ አድራሻችን ዝግጅቶቻችን መከታተል ትችላላችሁ። በሚቀጥለዉ ክፍል ድራማ እስክንገኛኝ በእዚሁ እንሰናበታለን ጤና ይስጥልን።**